# አገር እንዴት ሰነበተች? ቁጥር 5

የካቲት 5 ቀን 2014ዓም(12-02-2022)

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል በተከታታይ አገር እንዴት ሰነበተች በሚለው እርዕስ የሚቀርበው የዛሬው ቅንብራችን የሚከተለውን ይመስላል።

የአገራችን ሁኔታ በቀን ሳይሆን በዬሰዓቱ ብሎም በዬደቂቃው የሚለዋወጥ በመሆኑ ሁሉንም ለማካተት ያስቸግራል።ስለሆነም በዚህ ዓምድ ሥር ባለፉት ቀናት የታዩትንና የተሰሙትን ዋናዋና ክስተቶችና ድርጊቶችን ብቻ በማካተት ሌላው ቢቀር በታሪክ መዝገብ ቢቀመጡ ከማስረጃነት አልፈው ለትውልድ መማሪያ ይሆናሉ የሚል እምነት በመያዝ የምናዘጋጀው መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን። ሌሎቹም እንደኛው በዜና መልክ የሚዘግቡት ቢሆንም ፣እነሱ ይዘግቡታል ብለን የድርሻችንን እይታ አለማስቀመጡ ሃላፊነትንና ድርሻን መዘንጋት ስለሚመስለን በተጨማሪም ከሌሎቹ በኩል የሚቀርበውንም ባጋጣሚ ለመከታተል ያልቻለ ቢኖር እንዲያውቀው ይረዳል በማለት የምናዘጋጀው ቅንብር ነው።ተደጋግሞ መቅረቡም የሁኔታውን ክብደት ለማሳዬትና እንዳይዘነጋም ይረዳል።ከአንድ ወጥ ይልቅ ለተለያዩ አስተያዬቶችና ሃሳቦችም መፍለቅ በር ይከፍታል ብለን እናምናለን።

ባሳለፍናቸው ቀናቶች በአገራችን ውስጥ የተለያዩ ክንውኖችና ክስተቶች ታይተዋል።ከክንውኖቹ መካከል ትልቅ ትኩረት የተሰጠው የአፍሪካ ህብረት ዓመታዊ ስብሰባ ሲሆን ለቅንብሩ መሳካትና ለመሪዎቹም ደህንነት አገራችን ብዙ ወጭ አድርጋበታለች።ስብሰባው እንዳይሳካም በውጭ በተለይም አሜሪካ መራሹቹ አውሮፓ አገሮች ከጥቂት ተላላኪዎቻቸው የአፍሪካ አገሮች ጋር ጥምረት ፈጥረው ሽብር ሲነዙ መቆዬታቸው የሚዘነጋ አይደለም።ሆኖም ግን ሌሎቹ አገሮች ለሽብሩ ቦታ ሳይሰጡት በስብሰባው ላይ ተሳትፈዋል።ከአርባ ሽህ በላይ የጸጥታ ሃይሎች ተሰማርተው በመሪዎችና በተሰብሳቢዎቹና በታዛቢዎቹ ላይ ምንም አደጋ ሳይደርስ ስብሰባው በሰላም ተጠናቋል።በስብሰባው ላይ ያልተገኙ የጎረቤት አገራት መሪዎች ማለትም የኤርትራ፣የሱዳን፣የግብጽ፣ የሶማሊያ፣የሩዋንዳ፣የኡጋንዳ-----ወዘተ በአካል ባይሳተፉበትም በተወካዮቻቸው ተሰይመዋል።የስብሰባው አስተናጋጅ አገር ፣ የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ንግግር ያደረገ ሲሆን፤ንግግሩ የሱንና የሚመራውን መንግሥት ጥንካሬ የሚያጎላ፣ በአገሩ ውስጥ ሰላም እንደሰፈነ፣የእድገትና የልማት ጎዳና እንደተዘረጋ፣አገርና መንግሥቱ የተደቀነበትን የውስጥና የውጭ አደጋ እንደተወጣ፣በአረንጓዴው ዘመቻ ከ18 ቢሊዮን በላይ ችግኝ እንደተተከለና በቅርቡም ወደ 25 ቢሊዮን እንደሚደርስ አብራርቷል። ችግኝ ሲተከል ፣የፈጣሪ ችግኝ የሆነው የሰው ልጅ በገዛ አገሩ እዬተፈናቀለ፣በማንነቱ እዬተጨፈጨፈ መሆኑን፣ የሚመራው መንግሥት በሕገመንግሥት አጽድቆ በዘረጋው የጎሳ ፖለቲካ ምክንያት አገሩ የመኖር ህልውናዋ አደጋ ውስጥ እንደሆነች ግን ባይናገረውም የተሰበሰቡት ሁሉ በሚገባ ያውቁታል። ለአፍሪካ አንድነትና ሰላምም ተግቶ እንደሚሠራ ሳያፍር የገለጸ ሲሆን፣ሌሎቹ ባይናገሩትም በልባቸው"የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች" እንደሚሉት አንጠራጠርም። እራሱን፣የሰላማዊ አገር መሪ፣ የአፍሪካ ነጻ አውጭና ለአፍሪካ የቆመ ፓን አፈሪካኒስት አድርጎ ያቀረበበትም መንገድ የሚያስቅና የሚያስተዛዝብ ነው።ታዳሚዎቹ "ለማያውቁሽ ታጠኝ" ሲሉ ያልፉት ይሆናል እንጂ በንግግሩ ተመስጸዋል ብለን አናምንም።አብዛኞቹ ተመሳሳይ ችግር ውስጥ ስላሉም "እኛም ቤት እሳት አለ" በማለት ለመተቸት የደፈረ አልነበረም።

ይኸው ጉደኛ በአገሩ ውስጥ የጋዜጠኞችንና የሚዲያን ነጻነት የነፈገው አብይ አህመድ የአፍሪካ የሚዲያ ማእከል መቋቋም አለበት ሲል ለፍፏል። የአብይ ጨዋታና ማጭበርበር በዚህ ከለላ ሌሎቹ ያፍሪካ አገሮች ገንዘብ እንዲያዋጡ ለማድረግ መሆኑ ግልጽ ነው።ሌሎቹ አገራት ግን በዚህ ላይ የሰጡት አስተያዬት የለም፤የውይይት አጀንዳም ሆኖ አልቀረበም። ከቀናት በኂላምይህንኑ የጮሌ ሃሳቡን የሚያረጋግጥ ባለ 63 ፎቅ የሚዲያ ሴንተር ለማቋቋም ማሰቡና ሥራውን ለሚፈጽም ግለሰብ ከ5000ካሬሜትር በላይ ቦታ መስጠቱ ይፋ ሆኗል።

አገራችንና ሕዝቧ በመከራ ውስጥ እያሉ የእንዲህ አይነቱ አስረሽ ምችው፣ ወቅቱን ያላገናዘበ ፣አላፊነት የጎደለው በግንባታ ስም የዘረፋ ዕቅድ ሲነደፍ ለማንና ለነማን ጥቅም እንደሆነ ግልጽ ነው።በኢትዮጵያ ኪሳራ የመጭዋን የኦሮሚያን ሃገረመንግሥት የመገንባት አባዜ የፈጠረው ምኞት እንደሆነ አይካድም።

ሌላው የቀድሞው የዚምባብዌ መሪ የነበሩት ሮበርት ሙጋቤ ያነሱትን የአፍሪካ አገራትን በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት የመቀመጫ ወንበር ሙብትም በዚህ ስብሰባ ላይ አንስቶታል። የሚገርመው ነገር ግን የራሱ አገር ሕዝብ በኖረበት አገር መቀመጫ ማጣቱና ለዚያ መፍትሔ የሚሆን ሳይፈጥር ጭራሽ እዬተባባሰ እንዲሄድ በቀጥታና በስውር ተሳትፎ እራሱ በሚወክለው የኦሕዴድ ኦነግ ብልጽግና በሚያስተዳድረው መሬት ውስጥ ብቻ ሳይሆን አልፎ ተርፎ በራሱ አጽመ-ርስት የሚኖረው ኦሮሞ ያልሆነው ኢትዮጵያዊ በተለይም የአማራው ተወላጅ መሬቱን ለመያዝ ሲባል በዬቀኑ ሲታረድ፣ ሲፈናቀልና ንብረቱ ሲዘረፍና ሲወድም በአብይ አህመድ ኦሕዴድ የፕሮስፐሪቲ ተህስቦ የጽዳት እርምጃ ሆኖ ተወሰደ እንጂ ወንጀል ነው አልተባለም።ለተጨማሪ ጽዳትም በሙሉ ጉልበት እዬተሠራበት ነው። በዬቀኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንጹሃን በመጨፍጨፍ ላይ ናቸው።

የተሰበሰቡትን የአህጉሩን መሪዎች ያሳሰበው ዋናው ጉዳይ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ በምዕራብና መካከለኛው አፍሪካ አገራት ፣በማሊ፣በኢይቮሪኮስት፣ቦርኪናፋሶ የተካሄደው ወታደራው መፈንቅለ መንግሥት ሲሆን የዴሚክራቲክ ኮንጎ ፕሬዚዳንትም በሌሉበት በአገራቸው ሊካሄድ የታሰበውን መፈንቅለ መንግሥት ስጋት ለማምከን ከአንድ ቀን በኂላ ስብሰባውን አቋርጠው ሄደዋል።ደግነቱ የህብረቱን ሊቀመንበርነት ለተተኪው ለሴኔጋሉ መሪ ካስረከቡ በኂላ ሁኔታው መከሰቱና መሄዳቸው ነው። ይህ የአፍሪካ አገራትን የወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ዳግመኛ አባዜ የቀሰቀሰው የመሪዎቹ ድክመትና፣የሕዝቡን ጥያቄ የመመለስ ብቃት አለመኖር፣የሕዝቡ ችግርና ስቃይ እያደገ እንጂ እዬቀነሰ አለመምጣት፣የሃይማኖትና የጎሳ ተኮር ጥቃቶች መበራከታቸው በዋናነት የሚቀርብ ምክንያት ሲሆን የምዕራቡም የጥቅም ሽኩቻና የእጃዙር ቅኝ አገዛዝ መልሶ ማቆጥቆጥ ያመጣው መሆኑን የታዩት ዝንባሌዎች ያሳያሉ።በኮንጎው መሪ ላይ የታሰበው መፈንቅለ መንግሥት እውነት ከሆነ ምናልባትም ባለፈው ዓመት የሕብረቱ ሊቀመንበር በመሆን በአሜሪካኖችና በግብጾች ፍላጎት አንጻር ያስፈጽማሉ የተባሉትን የህዳሴን ግድብ ውይይት በተፈለገው መንገድ ባለማስፈጸማቸው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት በፖለቲካ ታዛቢዎች የተሰነዘረ ሲሆን የእኛም ግምት ከዚያ አይርቅም።የአሜሪካኖችና የምዕራባውያን ጣልቃ ገብነት እያደገ ከሄደ የወደፊቷ አፍሪካ ምን እንደምትመስል፣የአፍሪካ ህብረት የመኖር ያለመኖር እጣ ፈንታው ምን እንደሚሆን የምናዬው ይሆናል።አገራቱን በመከፋፈልና በማዳከም፣በጥቅም በመደለል የተሠሩ ሥራዎች እንዳሉም አይካድም። ጽ/ቤቱን ወደ ኬንያ ለመውሰድ የተደረገው ዘመቻ አንዱ ሲሆን ለጊዜው የቀዘቀዘ ቢመስልም ጨርሶ አልተወገደም።የዚህ ድርጅት መኖር ከፖለቲካና ከዲፕሎማሲው ጥቅም ባሻገር አንዱ የገቢ ምንጭ ስለሆነ ሁሉም አገር ለመውሰድ ቋምጧል።

በገዥው ፓርቲ ውስጥ መተራመሱና ክፍፍሉ ሌላው የሰሞኑ ትዝብት ነው። በሶማሊያው፣በአማራው ፣ በአፋሩ በኦሮሞው፣የብልጽግና መሪዎች መካከል አለመግባባትና ልዩነቶች ጎልተው ወጥተዋል።አንዱ

ሌላውን በማጋለጥ ላይ ነው።የሙስናው፣የዘረፋና የሌብነቱ ምስጢር አደባባይ ላይ ዝርግፍ ብሎ ወጥቷል።ይህንን ተከትሎ በቅርቡ  አንዱ የብአዴኑ -ብልጽግና አመራር አባል የሆነው አቶ ጸጋ አራጌ የተባለው ያቀረበው ባለስድስት ገጽ የማጋለጫ ሰነድ በሰፊው ተሰራጭቶ ሕዝብ ጆሮ ደርሶ እያነጋገረ ነው። ባቀረበው ደብዳቤ ላይ የብአዴን-ብልጽግና መሪዎች የአገዛዙ ተላላኪ መሆናቸውን፣ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ መከፋፈላቸውንና ከመቶ ሚሊዮን ብር ያላነሰም ባከኖ መቅረቱን ሳይደብቅ አጋልጧል። ማጋለጡ በብአዴን ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ብልጽግና በሚሉት ስብስብ በሙሉ በተለይም በመሪው በአብይ አህመድ ግለኝነትና ፈላጭ ቆራጭነት አሠራር ላይ ሰፊ ማብራሪያ የሰጠ ነው። የባለሥልጣኑን የገንዘብ ብክነት ማጋለጥ ተከትሎ በባአዴን መሪዎች ውስጥ ጭቅጭቅ ተነስቷል። ጭቅጭቁ በተከፋፈሉት መሃል ሲሆን የክፍፍሉ ዝርዝር በመውጣቱና በመታወቁ  በድርሻ ዙሪያ ያስነሳው ንትርክ ነው። ወትሮም ሌባ ሲሰርቅ ይስማማል፣ሲካፈል ይጣላል ነውና አይደንቅም።ወያኔ እዬወረረ ሲገሰግስ አገሪቱን ሙሉ ለሙሉ የሚቆጣጠር መስሏቸው “ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አንተም ዝረፍ” በሚለው ብሂል ሃፍረተቢሶቹ የብአዴን መሪዎችም የቻሉትን ዘርፈው ለመውጣት ያቀዱበት የሌብነት ድርጊት እንደሆነ ሁሉም ተገንዝቦታል።የወያኔ ጉዞ ሲጨናገፍ ድርጊታቸው አደባባይ ላይ ሲወጣ ያቀረቡት መከላከያ ግን ከስርቆቱ በላይ የሚያዋርዳቸው ሆኗል።የወሰድነው በብድር ነው ሲሉ ዓይናቸውን በጨው አጥበው ብቅ ብለዋል።ብድር ነው የሚለውን ብንቀበል እንኳን አገኘሁ ተሻገር የወሰደውን 9 ሚሊዮን ብር እንዴት አድርጎ ይከፍለዋል ብለን ስንጠይቅ ፣የሚያገኘው የወር ደመወዙ ከነጥቅማ ጥቅሙ 40,000ሽህ ብር ይሁን ብንል በዓመት 480,000  ማለት ነው ፤የተበደረው ገንዘብ ወለድ በትንሹ 10% ቢሆን ፣የዓመት ወለዱ ብቻ 900,000 ሽህ ብር ይሆናል።ታዲያ እንደ ኳስ በአዬር እዬተሞላ የሚንቀሳቀስ ቢሆንና ሁሉንም ገቢውን ለዕዳው ወለድ ከፈለ ቢባል እንኳን፣ መክፈል ከሚኖርበት ጠቅላላ ወለድ ሲቀነስ የ420,000 ዕዳ አለበት ማለት ነው።ታዲያ ባንኮች የሚያበድሩት ለሰማይ ቤት ብለው ይሆን ወይስ አገኘሁ ተሻገር ከሕግ ውጭ እንዲጠቀም ብለው ከመደበኛ የወለድ ገደብ በታች ያስቀመጡት ተመን አለ?።ለመሰረቁ ይህ እራሱን የቻለ ማስረጃ ነው። የሌሎቹም እንዲሁ!

ይህንን ወንጀል ለመሸፋፈን ሲባል  በአጋላጩ  የፓርቲው አባል በአቶ ጸጋ አራጌ ላይ ግን የተሰጠው መግለጫ በጣም የወረደና የሰዎቹን ልክስክስነት ይበልጥ ያጋለጠ ነው። ቀውሱ በዚህ የሚቆም አይመስልም እንደ ፒራሚድ ተያይዞ መንኮታኮቱ የማይቀር ዕዳ ነው።

በተመሳሳይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩም ውስጥ እንዲሁ አንዲት ደፋር፣ፈቲሃ ሙሃመድ የተባለች ወጣት የብልጽግና ተመራጭ የምክርቤቱ አባል ፣ከንቲባዋ አዳነች አቤቤና የኦሕዴዱ የኦሮሞ ክልል ተብዬው መሪ ሽመልስ አብዲሳ በተገኙበት፣ በአዲስ ቴሌቪዥን በቀጥታ በሚያስተላልፍበት የስድስት ወር የሥራ ግምገማ  ስብሰባ ላይ  ሁሉንም ባለሥልጣኖች ያናደደ ንግግር አድርጋለች። ካደረገችውም ንግግር  ከድጡ ወደማጡ እዬሄድን መሆኑ ያስታውቅብናል፤ጁንታን ከሰሜን ነቀልን ስንል መልሰን  ማንም አይጠይቀኝም የሚል ሌላ ጁንታ በአዲስ አበባ ተተክሏል።ሃሳባችንን በነጻ ልንገልጽ አልቻልንም፤ታፍነናል፤በማስፈራሪያና ዛቻ እንድንሸማቀቅና ጸጥ እንድንል ሆነናል---ወዘተ በማለቷ ንግግሯ ለሕዝቡ እንዳይደርስ የነበረው የቀጥታ ስርጭት ተቋርጧል።ሌላም አባል አስተዳደሩ ለተማሪዎች ቁርስ በዓመት 1,9 ቢሊዮን ብር አወጣሁ ባለው ላይ ወጭው ከአዲስ አበባ ውጭ በዙሪያ ያሉትንም የኦሮሞ ትምህርት ቤቶች ያጠቃለለ ነወይ ?ብለው ላቀረቡት ጥያቄ  የተበሳጨው  የላፍቶ ክፍለ ከተማ የብልጽግና ተመራጭና ፣የአስተዳደሩ  ትምህርት ቢሮ ሃላፊ የሆነው ዘላለም ሙላቱ የተባለው ስድ ለጥያቄው ተገቢ መልስ ከመስጠት ፈንታ ተንደርድሮ አዲስ አበባ ከርሷን ሞልታ ፈርሷን የምትደፋው ኦሮሚያ ላይ ነው በማለት ከጉዳዩ ጋር ያልተያያዘ የከተማዋን ንዋሪ ሕዝብ የናቀና ያዋረደ ስድብ ብቻም ሳይሆን የጥላቻ መርዝና ግጭት ቀስቃሽ የሆነ መልእክት ሰንዝሯል።በስብሰባው ሊቀመንበርም  በዝምታ ታልፏል። በአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ ጥላቻና ንቀት ሲሰማ ይህ የመጀመሪያ

አይደለም።ከዚህ በፊትም አንጋሳ የተባለ ብልጽግናን ወክሎ የብሔራዊ ምክር ቤቱ አባል ሆኖ የተመረጠ ባለጌ የአዲስ አበባ ሕዝብ ከኮንዶም ያመለጠ የሽርሙጣ ልጅ ነው ብሎ ነበር።የአሁኑም ባለጌ ሰው ድፍረት በዚያ ሰው ላይ የደረሰ ቅጣትም ሆነ ነቀፋ ከመንግሥት በኩል ባለመኖሩ ማን ይነካኛል ከሚል የተረኞች ትእቢት የተነሳ ነው እንላለን።ነገም ሌላው ባለጌ እንዲሁ በአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ ሲያቀረሽበት እንሰማ ይሆናል። የአዲስ አበባ ነዋሪ መብቱን ካላስከበረ የደንቆሮና የባለጌዎች መፈንጫ ሆኖ ይቀራል።ከዛም አልፎ ተርፎ ይህ ለቀጣዩ የከፋ እርምጃ ማለማመጃ ሊሆን ይችላል።በስብሰባው ላይ አዲስ አበባ የሚለው ስያሜ በተደጋጋሚ ፊንፊኔ በሚለው መለወጡም ሌላው የማለማመጃ ስልት ሆኖ ታይቷል።

ሥርዓቱ በአቶ ጸጋ አራጌና በፈቲሃ ሞሃመድ ላይ ምን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል ባይታወቅም በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ግን ሳያጠቃቸው እንደማይቀር ያለፉት ታሪኮቹ ያረጋግጣሉ። ሌሎቹም አገር ወዳዶች ጥንቃቄ እንዲያደርጉና የኢትዮጵያ ሕዝብም ለእውነት የቆሙ ልጆቹን ከአደጋ የመጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ እናሳስባለን።

አንድ መንግሥት ውድቀት ደረጃ ላይ ሲደረስ የዚህ አይነቱ የውስጥ መፋተግ፣መወነጃጀልና ማጋለጥ እንዲሁም ዓይን ያወጣ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተለመዱ ናቸው።የብልጽግናን የወደፊቱን የውድቀት ጉዞ ለመተንበይ አመላካቾች ብቻ ሳይሆኑ መንደርደሪያዎች ናቸው።

ለአፍሪካ መሪዎች ደህንነት ሲል ከ40 ሽህ የጸጥታ ሃይል በአዲስ አበባ ብቻ ያሰለፈ መንግሥት በወለጋ፣በቤንሻንጉል፣በአማራውና በአፋሩ ብሎም በቅርብ እርቀት ላይ በሰሜን ሸዋ የተንሰራፋውን የአሸባሪዎች የጥፋት ሃይል ለመቋቋም ፍላጎት አላሳዬም። ይህንን የመንግሥት ድክመት ብቻ ሳይሆን ምን አገባኝነት ተከትሎ ትግራይ ውስጥ ተቀርቅሮ የነበረው የወያኔ የጥፋት ሃይል የልብ ልብ ተሰምቶት ከዋሻው ወጥቶ ፣የተከዜን ወንዝ ተሻግሮ ለዳግመኛ ጊዜ የወሎና የአፋርን ሕዝብ በመውረር ካለፈው ጊዜ የከፋ ግድያ፣ውድመትና ዘረፋ ለመፈጸም ዕድል አግኝቷል። የአማራና የአፋር ሕዝብ በወያኔ ወራሪ ሃይል በከባድ መሳሪያ እዬተደበደበ የድረሱልን ጥሪ ሲያስተጋባ የአብይ አህመድ መንግሥት ለጥሪው ተገቢ መልስ ሰጥቶ ሕዝቡን ከጥፋት አላዳነም።የወያኔ ወራሪ ሃይል ቦታዎችን እዬተቆጣጠረ በመገስገስ የጅቡቲን በር ለመዝጋት ሲቃረብያገሪቱ መከላከያ በምን አገባኝነት ተቀምጦ እያዬ ነው።ይህ ዝምታ በአገሪቱ የመከላከያ ሃይል መኖር አለመኖሩን ጥያቄ ውስጥ ከቶታል። በሌላውም ያገሪቱ ምዕራባዊ ክፍል የኦነግ አሸባሪ ቡድን ወደ ሃይልነት ተቀይሮ የቁጥጥር መረቡን በተለያዩ ቦታዎች ካለምንም ችግር ሲዘረጋ፣በወለጋና ባካባቢው ንጹሃንን እያረደ የጎጃምን መንገድ ዘግቶ ሹፌሮችን እዬገደለና እዬዘረፈ፣ ከባድ መሣሪያዎችን ታጥቆ ሲገሰግስ፣የኬንያን ድንበር መውጫ መግቢያ ኬላ ተቆጣጥሮ ግብር ሰብሳቢ ሆኖ ባለበት ዝም ብሎ መመልከቱ የአገሪቱ መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን የሽብር ቡድኑ አካል መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ይሉኝታ ቢሱ አብይ አህመድ የጸጥታ አባላቱን በወዳጅነት መናፈሻ(ፓርክ) ውስጥ ሰብስቦ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ኩራት መሆናችሁን ያፍሪካ መሪዎች አረጋግጠዋል ሲል ሸንግሏቸዋል።

የኦነግ ዙሪያ ገጠም እንቅስቃሴ በአዲስ አበባም ሰማይ ላይ የስጋት ድባብ አስፍኗል።ዘረፋው፣ ስርዓተ አልበኝነቱ፣ስጋቱ፣አለመተማመኑ፣የተረኝነት ስሜቱ---ወዘተ ሲደመር የነገው የከተማዋ ነዋሪ ሕዝብ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ሲያስቡት ይዘገንናል።

ይህንንም በመከተል ይመስላል አሁንም ኢትዮጵያን ለቃችሁ ውጡ፣ወደ ኢትዮጵያም አትሂዱ የሚለው የአሜሪካኖች ጥሪ ዳግም ያገረሸበት። የአሜሪካኖቹ አቋም ከጊዜው ጋር የሚለዋወጥ መሆኑን ባለፈውም መግለጻችን አይዘነጋም።ወያኔና ኦነግ በተጠናከሩ ጊዜ ማእቀብ በመጣልና በማስገደድ ብሎም ሽብር

በመንዛት ስውር ድጋፋቸውን ሲሰጡ የታዘብነው ነው።ወያኔና አጋሮቹ ሲዳከሙ የአሸናፊው ወገን ደጋፊ የመሆንም አዝማሚያ አሳይተዋል።አሁን መልሶ የአሸባሪዎቹ ሃይል ተጠናከረ ብለው ሲያስቡ ደግሞ ያንኑ ካርታቸውን መዘው ብቅ ብለዋል።ለተጨማሪ ማስገደጃ የማእቀብ ሕግ ነድፈው ማጽደቃቸው ተሰምቷል።በአብይ አህመድ መንግሥት በኩል የነበረው አለመግባባት ተወግዷል የሚል የውሸት ወሬ ቢሰራጭም የቻይናዎችና የሌሎቹ የጥቅም ባላንጣዎቻቸው ከአፍሪካ ብሎም ከኢትዮጵያ መሬት ካልተወገዱ አሜሪካኖችና ተባባሪዎቻቸው  እንደማይተኙ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል። ለጥቅማቸው ሲሉ ሌላው አገር ቢፈራርስ፣ ሕዝቡ እርስ በርሱ ቢያልቅ ቢተላለቅ ደንታ የላቸውም። የሩቁም የቅርቡም ታሪካቸው የሚያሳዬው ይህንኑ እውነታ ነው።ከያንዳንዱ መፈንቅለ-መንግሥት ጀርባም የነሱ መኖር አይካድም።

መንግሥት ተብዬው አጭበርባሪ ቡድን አሁንም ማታለሉን አላቆመም።ከአሸባሪዎች ጋር ንግግር አልጀመርኩም እያለ ሲቀደድ፣በሌላ ቦታ ንግግር በማድረግ ላይ መሆኑን ያበስራል።የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣኖች የንግግሩን መኖር በኤምባሲ በኩል ተነግሮናል የሚለው ወሬ ከፓሪስ ብቅ ሲል፣ የዓለም መንግሥታት ድርጅት ምክትል ዋና ጸሓፊ የሆነችው ወ/ሮ አሚና ሞሃመድ ገና ከአገር ሳትወጣ ቦሌ አዬር ማረፊያ ላይ በሰጠችው መግለጫ መንግሥትና የወያኔ አሸባሪ ቡድን በንግግር ላይ መሆናቸውን ይፋ አድርጋለች።ሴትዮዋ በከረመችበት የሳምንት ቆይታዋ ትግራይ፣ወሎና አፋር ጭምር ስትዘዋወር የቆዬች ሲሆን ከወያኔ መሪዎችም ጋር ተገናኝታ ያረጋገጠችው ብቻ ሳይሆን ምናልባትም በንግግሩ ሂደት ውስጥ ሳትሳተፍ እንዳልቀረች የሚያመላክተው የሰጠችው መግለጫ ነው።እውነት ባይሆን ኖሮ  መንግሥት ከሕዝቡ ሸሽጎ  በሚስጥር የያዘውን ጉዳይ በአደባባይ አትዘረግፈውም ነበር።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሲኖዶስና በከተማዋ ከንቲባ መካከል በየካቲት 4 ቀን ሊደረግ ታስቦ የነበረው ንግግር በከንቲባዋ አይመቸኝም ባይነት ሳይካሄድ ቀርቷል።ለሁለተኛ ጊዜ አሻፈረኝ ያለችውን ከንቲባ የሦስተኛ ጊዜ ዕድል በመስጠት ለሚመጣው ማክሰኞ ለየካቲት 8 ቀን 2014 እንድትቀርብ ቢወሰንም መምጣት አለመምጣቷ ግን በእለቱ የሚታወቅ ይሆናል።በመካከሉ አብይ አህመድ  በበኩሉ ፓትሪያርኩን ለማናገር ማሰቡ የተሰማ ሲሆን ከበስተጀርባ ያዘለው ሌላ ማደንዘዣ ይኖራል ተብሎ ይጠረጠራል።ሆነም ቀረም ሲኖዶሱ በአቋሙ ጸንቶ የቤተክህነቷንና የሕዝበ ክርስቲያኑን ክብርና መብት አሳልፎ ላለመስጠት ጠንክሮ መሄድ ይጠበቅበታል።ለመስቀል አደባባይ የባለቤትነት መብት ብቻም ሳይሆን  ለወደሙት ቤተመቅደሶች፣ንብረቶችና ለታረዱና ለተፈናቀሉት ምእመናን  ተጠያቂውን አካል በሕግ እንዲያቀርብ መንግሥትን መጠዬቅ መረሳት የለበትም እንላለን።

ተወደደም ተጠላ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነው አገር ወዳዱ ሕዝብ ፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶና የሰላማዊው እስልምና ፣እንዲሁም የሌላው እምነትና ፍልስፍና ተከታይ የሆነው ዜጋ፣በተለይም እንዲጠፉ የተፈረደበት የአማራው ተወላጅ ያለው የመጨረሻ ዕድል የሚመጣውን አስፈሪ  አደጋ ለመቀልበስ የሚችለው አንድ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዞ በሚያደርገው የሞት የሽረት ትግል መሆኑን ተገንዝቦ ሲደራጅና ሲታገል መሆኑን ልብ ሊለው ይገባል።በመካከሉ ልዩነት እንዲኖርና እርስ በርሱ ተከፋፍሎ ሃይሉ እንዲዳከም የሚሠሩትን  የውስጥና የውጭ ባንዳዎች በማሶገድ ለጠላቶቹ መግቢያ ቀዳዳ ሊነፍጋቸው ይገባል።እሱን መስለው ሰርገው የገቡ ተላላኪዎችንና የዘረፋ ቡድኖችን ለይቶ ማሶገዱ ለራሱ ዕድሜና ለትግሉ ውጤት ወሳኝ ሚና አለው።የመጣው አደጋ የሁሉም ስለሆነ አይመለከተኝም ወይም እኔ እተርፋለሁ በሚል ቀቢጸ ተስፋ ደንዝዞ መቀመጥ ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል። በታሪክም ያሳፍራል።

በአልበገር ባዩ በአፋሩና በአማራው በኩል ያለውን  የፋኖ ሃይል በመቀላቀል ሁሉም አገራዊ ተልእኮውን እንዲወጣ  የተለመደ ጥሪያችን ነው።ፋኖ ሕዝባዊ ሃይል እንጂ ለአንድ ጎሳ ብቻ የሚታገል

ቡድን አይደለም።እንዳይሆንም ለማድረግ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው።የታጠቀን ጠላት ማሳገድ የሚቻለው በትጥቅ እንጂ በልመናና፣በጸሎት አይደለም።ስለሆነም ገዝቶም ሆነ ማርኮ መታጠቅ ግዴታ ነው። በአካል ለመሳተፍ የማይችለው አገር ወዳድ ትግሉን በገንዘብ፣ በቁስና በፕሮፓጋንዳ ዘመቻ መሳተፍ ፤የተፈናቀሉትን መርዳትና ማቋቋምም የትግሉ አካል ሆኖ መታዬት አለበት እንላለን። ለከፉም ለደጉም ደግመን ደጋግመን ልናሳስብ የምንወደው የአሸባሪዎቹን ክንድ ለመስበርና እራስን አድኖ ኢትዮጵያን ለመታደግ መደራጀትና መታጠቅ አስፈላጊ መሆኑን ነው።መደራጀትና መታጠቅ ያስከብራል።የተደራጀና የታጠቀ ይከበራል፣ያባርራል። ያልተደራጀና ያልታጠቀ ይደፈራል፣ይታረዳል፣ ይባረራል። ስለሆነም

የምን እዬዬ ነው የምን አንገት መድፋት፣

ታጥቆ መሰለፍ ነው፣ ገፊውን ለመግፋት፣

አጥቂውን ለማጥቃት፤አጥፊውን ለማጥፋት።

መንግሥት ባዘጋጀው የሰላም ውይይት ተማምኖ መቀመጥም ለጠላቶች ፍላጎት ለማስጎብደድ እንጂ ለሚፈለገው አገራዊ አንድነትና ሰላም እንደማይረዳ ካሁኑ በመንግሥት በኩል የተሰጠው ገደብ ያሳያል።የማይነኩና ለውይይት የማይቀርቡ ናቸው ብሎ ካስቀመጣቸው ውስጥ ሕገመንግሥቱ፣የክልል አስተዳደር መዋቅሩና ሰንደቅ ዓላማው መሆናቸውን አፈንፍኖ ለማወቅ እረጅም አፍንጫ ያለው ፖለቲከኛ መሆን አያስፈልግም።

በእኛ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረገው ትግል ለተሻለኑሮ፣ለእኩልነትና ፍትሕ፣ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መስፈን እንጂ ሰንደቅ ዓላማ ይቀዬርልኝ፣የክፍለሃገር አወቃቀር በጎሳ ተኮር ክልል ይለወጥልኝ፣ ሁሉም የሚግባባበት ባለፊደሉ አማርኛ ቋንቋ ይወገድልኝ ብሎ አልነበረም፣አሁንም አይደለም። ስለሆነም የሰላም ውይይቱ ሂደት እነዚህን ከግምት ውስጥ እንዲያስገባና የአገሪቱን አንድነትና የሕዝቡን ሰላማዊ ኑሮ ያናጋውን የጠባብ ብሔረተኞችን ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ሕዝብ የሆነ ፍላጎት ቦታ እንዳይሰጠው ከወዲሁ ልናሳስብ እንወዳለን።ለዘላቂ ሰላምና ለችግሩ መፍትሔ ብሎም ለወደፊቱ ዋስትና ወንጀለኞችን ለይቶ በፈጸሙት ልክ ቅጣታቸውን ማግኘት እንዳለባቸው ማመን ያስፈልጋል። ውይይቱ በኢትዮጵያዊነት ካስማ ላይ የቆመና የሚያጠነጥን መሆን አለበት።በኢትዮጵያዊነቱ የማያምንና ለኢትዮጵያ አንድነት ደንታ የሌለው፣ኢትዮጵያን አፈርሳለሁ ብሎ የተነሳ፣ሰላም ያደፈረሰ ቡድን የውይይቱ አካል ሆኖ መቅረብ አይኖርበትም ።ለውይይቱ ስኬታማ መዳረሻ አንድ የጋራ መነሻ መኖር አለበት እንላለን።ያም ኢትዮጵያዊነት ነው!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!